## *የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከተቋቋመ ጀምሮ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት*

- የሌሎች አገሮችን ምርጥ ተሞክሮ በማጥናት ዘርፉን ለማሳደግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ረቂቅ በማዘጋጀት በመንግሥት እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡
- የማኅበረሰብ ሬዲዮ በአገራችን ለማስፋፋት የሚያስችል አሰራር ተዘርግቶ ፈቃድ የመስጠት ሥራ ተጀምሯል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ለ10 ማህበረሰብ ሬዲዮ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ ከነዚህ ውስጥም ስምንት የማኅበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያዎች **ሙሉ** ስርጭት የጀመሩ **ሲሆን** የሰቲት ሁመራ እና የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያዎች ስርጭት ለመጀመር በዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡
- ለበርካታ አመታት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ብቻ የነበረው የብሮድካስት አገልግሎት የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍበት አስፈላጊውን አሰራር በመዘርጋት ፈቃድ የመስጠት ሥራ ተጀመሯል፡፡
- ቀደም ሲል ሥራ ላይ የነበሩ 2 ሬዲዮ ጣቢያዎች ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሥራ ከጀመረ በኋላ በንግድ ብሮድካስተርነት ተመዝግበዋል፡፡



- በአዲስ አበባ ከተማ ለ4 የንግድ ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎች ፈቃድ ተሰጥቶ 4ቱም ሥራ ጀምረዋል፡፡
- ቀደም ሲል በማዕከላዊ መንግሥት ብቻ በባለቤትነት ተይዞ የነበረውን የብሮድካስት አገልግሎት ክልሎችም ባለቤት የሚሆኑበት አሰራር ተዘርግቶ በአሁኑ ጊዜ 6 ክልሎችና 2 የከተማ መስተዳድሮች የራሳቸው ሬዲዮ ጣቢያ አቋቁመዋል፡፡
- የኦሮሚያ ክልልና የድሬደዋ ከተማ መስተዳድ**ር የራሳቸውን** የቴሌቪዥን ጣቢያ በማቋቋም ስርጭት **ጀምረዋል**፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድ**ር** የቴሌቪዥን ጣቢያ የሙከራ ስርጭቱን እያከናወነ ይገኛል፡፡ የሐረሪ እና የሶማሌ ክልል የቴሌቪዥን ፈቃድ ወስደው ስርጭት ለመጀመር በቅድመ ዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡
- ሁለት የውጭ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን ተቀብለው በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ አገልግሎት ሰጪ አካላት ፕሮግራሞቻቸውን በማሰራጨት ላይ ይገኛሉ፡፡
- የሬዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎች የሕብረተሰቡ መብትና ፍላጎቶች አክብረው መስራታቸውን ለመከታተል የሚያስችል በብሮድካስተሮች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችና ጥቆማዎች ማስተናገጃ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡
- 192 ከአንድ ክልል በላይ የሚሰራጩ የሕትመት ውጤቶች ተመዝግበዋል፤



# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# The Federal Democratic Republic of Ethiopia

## የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን
## Ethiopian Broadcasting Authority
## አጠቃላይ መረጃ

ስልክ (Tel): 251-115538760/59
ፋክስ (Fax): 251-115536750
ኢ.ሜይል (E-mail): e.b.a1@ethionet.et
ዌብሳይት (Website): www.eba.gov.et
የመ.ሣ.ቁ. (P.O.Box): 43142

## የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን **በተ ሻሻለው የብሮድካስት አዋጅ ቁጥር** 533/99 የተቋቋመ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት ነው፡፡ መ/ቤቱ ሥራውን ከጀመረበት ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

### ራዕይ

ብዙኃዊነቱና ተደርሽነቱ የተረጋገጠ በኃላፊነት መንፈስ የሚሠራ የመገናኛ ብዙኃን በመላ ሀገሪቱ ተስፋፍቶ ማየት፤

### ተልዕኮ

የምዝገባና ፍቃድ አገልግሎት በመስጠት እንዲሁም በዘርፉ ተገቢውን የጥናት ፣የድጋፍና የክትትል ስራዎች በመስራት ለአገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት አስተዋጽኦ የሚያበረክት ፣ጥራቱ የተጠበቀ ቀልጣፋና አስተማማኝኝ የመገናኛ ብዙኃን እንዲስፋፋ ማድረግ፣



ጥቅምት 2004ዓ.ም

## የባለሥልጣኑ ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነቶች

- የብሮድካስት አገልግሎት ለአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ተገቢውን አስተዋፅኦ ሊያበረክት በሚችል መልኩ መካሔዱን ማረጋገጥ፣
- የብሮድካስት አገልግሎት የሬዲዮ ሞገድ ዕቅድ በማዘጋጀት ለብሮድካስት አገልግሎቶች ፈቃድ መስጠት፣
- ለብሮድካስት አገልግሎት የሚውሉትን መሣሪያዎች ዓይነትና ደረጃ፣ የማሠራጫ መሣሪያውን ጉልበት እንዲሁም የብሮድካስት ጣቢያ የሚቋቋምበትን ሥፍራ የሽፋን ክልል መወሰን፣
- ስለብሮድካስት አገልግሎት ዕድገትና መሻሻል ጥናት ማድረግና አገልግሎቱን የሚመለከቱ መረጃዎችን አጠናቅሮ መያዝ፣
- የብሮድካስት አገልግሎት መሣሪያዎችንና የቴክኒክ ደረጃዎችን ማውጣት፣ ለመሣሪያዎቹ አስመጪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት፣
- በብሮድካስት አገልግሎት በሚነሱ ቅሬታዎች ላይ ውሳኔ መስጠት፣
- ከአንድ ክልል በላይ የሚሰራጩ የሕትመት ውጤቶችን መመዝገብ፣

## የመ/ቤቱ ተጠሪነትና አደረጃጀት

### ከመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ  ጥናት በፊት

ባለስልጣኑ መ/ቤት በአዋጅ ሲቋቋም ተጠሪነቱ ለጠቅላይ



ጥቅምት 2004ዓ.ም

ሚኒስትሩ የነበረ ሲሆን በኋላ አሠራሩን ለማቀላጠፍ ሲባል ተጠሪቱ ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ሆኖ ቆይቷል፡፡

ከመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ጥናት በፊት የነበረው አደረጃጀትም፡-

ቦርድ፣

↓ ዋና ዳይሬክተር፣

↓ ም/ዋና ዳይሬክተር፣

↓ አስፈላጊ ሠራተኞች ያሉት ነበር፡፡

***መሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ጥናት በኋላ የመ/ቤቱ አደረጃጀት***

ቦርድ፣

↓ ዋና ዳይሬክተር፣

↓ ም/ዋና ዳይሬክተር፣

↓ የሥራ ሂደቶችና አስፈላጊ ባለሙያዎች

የባለሥልጣን መ/ቤቱ ከመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ጥናቱ በኋላ የዚህ ዓይነት አደረጃጀት ሲኖረው በሚኒስትሮች ምክር ቤቱ ደንብ ቁጥር 158/2001 መሠረት ቀድሞ ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ተሰጥቶ የነበረው የሕትመት ምዝገባ ሥልጣን ለባለሥልጣኑ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ ደንብ ቁጥር አንቀጽ 11/2 መሰረትም የባለሥልጣኑ መ/ቤት ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆኗል፡፡

የሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ